የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለ የሥነምግባር

መመሪያ ቁጥር 578/2013

መጋቢት 2006

መግቢያ

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚመሩባቸውና የሚተገብሯቸውን የስነምግባር መርሆችን በግልፅ በማስቀመጥ ሙስናን የሚጠየፍና የሚዋጋ፣ መልካም ስነምግባር ያለው ሰራተኛ በመፍጠር ዜጎች በመስሪያቤቱ አሰራሮችና በሚሰጡት አገልግሎቶች ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ለማድረግና የስነምግባር መስፈን ለተቋሙ የግብ ስኬትና ደንበኞችን ለማርካት የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚመሩበትን አንድ ወጥና ዘመናዊ የሆነ የሥነ ምግባር መርሆዎችና ግዴታዎችን የሚወስንና እነዚህም ተጥሰው ሲገኙ የሚወሰዱትን የዲሲፕሊን ቅጣቶች የያዘ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 እና ስለፌደራል መንግስት ሰራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ ሥነሥርዐት የወጣ የሚንስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው የኤጀንሲው ስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ወጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የሠራተኛ የሥነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 578/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በደንብ ቁጥር 261/2004 የተቋቋመው የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
2. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡
3. "ኃላፊ" ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር፣ የዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮችና ሌሎች የስራ ኋላፊዎች ናቸው፡፡
4. "ሠራተኛ" ማለት በመ/ቤቱ ውስጥ በቋሚነትና በኮንትራት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡
5. "ቤተሰብ" ማለት የመንግስት ሰራተኛው ሚስት፣ ባል፣ ልጆች እንዲሁም በሰራተኛው ስር የሚተዳደሩ ሌሎች ሰዎች ናቸው፡፡
6. "ቅርብ ዘመድ" ማለት የመንግስት ሰራተኛው እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነው፡፡

7. "ሀብት" ማለት የዳይሬክተር፣ የአገልግሎት ኃላፊ ወይም የሰራተኛው ወይም የቤተሰቡ ማንኛውም ገቢ፣ ቁጠባ፣ ኢንቨስትመንት የመሬት ይዞታ ወይም ሌላ ንብረት ነው፡፡

8. "ገቢ" ማለት ደመወዝ፣ ከግል ድርጅት፣ ሽርክና፣ ከአክሲዮን የሚገኝ ትርፍ፣ የሎተሪን ገቢ፣ የቁጠባ ገቢና የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

9. "የጥቅም ግጭት" ማለት የኤጀንሲው ሠራተኛ ወይም የቤተሰቡ፣ የቅርብ ዘመዱ ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ትስስር ወይም ቁርኝት ያለው የገንዘብ ወይም ሌላ አይነት ጥቅም ከመደበኛ ስራው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሲሆን ነው፡፡

10. "ስጦታ" ማለት የኤጀንሲው ሠራተኛ በሠራተኛነቱ ምክንያት ለሰጠው አገልግሎት የተሰጠው የገንዘብ ወይም ማንኛውም የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው፡፡

11. "መስተንግዶ" ማለት የኤጀንሲው ሠራተኛና ኃላፊ ወይም ለቤተሰቡ በሰራተኛነቱ ምክንያት የተደረገለት ነጻ የሆነ የምግብ፣ የመጓጓዣ የሆቴል ወይም ሌላ ዓይነት የመዝናኛ አገልግሎት ነው፡፡

12. "ተገቢ ያልሆነ ባሕርይ" ማለት ኤጀንሲው ከሚከተለው ማንኛም ህግ ደንብ እና የአሠራር መመሪያ ጋር የማይጣጣም ማናቸውም ባሕርይ ነው፡፡

13. "የሥነ ምግባር ብልሹነት" ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የሥነምግባር መርሆዎችን ወይም እሴቶችን የሚቃረን ድርጊት ወይም ባሕርይ ነው፡፡

14. "ጥቆማ ማቅረብ" ማለት በመ/ቤቱ ውስጥ የሚፈጸም ተገቢ ያልሆነ አሠራርን ወይም የሥነምግባር ብልሹነትን በሚመለከት በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በማንኛውም መንገድ የሚቀርብ መረጃ ወይንም አስተያየት ነው፡፡

15. "የሥነ ምግባር መኮንን" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ውስጥ የሥነ ምግባር ጉዳዮችን እንዲከታተል የተቀጠረ የኤጀንሲው ሠራተኛ ነው፡፡

16. "የስነምግባር መከታተያ ክፍል" ማለት በመ/ቤቱ የስነምግባር ሁኔታን የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል ነው፡፡

አንቀጽ 3.የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በኤጀንሲው ውስጥ በሚሠራ ማንኛውም የስራ ኃላፊና ሰራተኛ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል ፡፡

አንቀጽ 4.የኤጀንሲው ግዴታዎች

1. ማንኛውም ሰራተኛ ይህንን መመሪያ እንዲያውቅ ለማድረግ

ሀ. ለኤጀንሲው ሰራተኞች የስነምግባር ትምህርትና ስልጠና መስጠት

ለ. የስነምግባር መመሪያውን አባዝቶ ለሰራተኞቹ መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል

ሐ.ስላጋጠሙ የሙስና እና ጉልህ የሆኑ የሥነ ምግባር ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች ለፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት ማቅረብ፡፡

አንቀጽ 5.የሥነ ምግባር መኮንን ሥልጣንና ተግባር

የሥነ ምግባር መኮንኑ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል አሠራርን ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 144/2000 የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ክፍል ሁለት

የሥነምግባር መርሆዎችና የዲሲፕሊን ጥፋቶች

አንቀጽ 6.ቅንነት

ቅንነት ማለት የተሟላ ስብዕና ጠንካራ እምነት ጽኑ አቋምና ሃቀኝነትን የሚሳይ ወይም የተሟላ ስብዕና ያለው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ሃላፊዎች፡-

1. ከሕዝቡ ጋር የሥራ ግንኙነት በሚያደርጉበት፣ በሙያ የሚያገለግሉበትና የግል ሕይወታቸውን በሚመሩበት ጊዜ የሕዝቡን አመኔታ በሚጠብቅና በሚያጠናክር አኳኋን ህብረተሰቡ በመ/ቤቱ ላይ እምነት ሊያሳድር በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ጥሩ ምግባር በማሳየት ሥራቸውን በጥበብ/በሥርዓት/፣ በጥንቃቄ፣ በትጋት፣ በሙሉ ጉልበት፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ አኳኋን መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ህግን ተከትለው የተቀጠሩበትን ሥራ ማከናወንና ተገቢ ያልሆነ አድራጎት ከመፈጸም መራቅ አለባቸው፡፡
4. ለሙያቸውና ለስራቸው ጠቃሚ የሆኑ አሰተያየቶችንና አሰራሮችን ከተገልጋዮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለመማር ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ ፣ /2/ ፣ /3/ እና /4/ ሥር የተጻፉትን ባለማክበር የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

   ሀ. የኤጀንሲውን መልካም ስም የሚጎዳ ወይም ህዝቡ በኤጀንሲው ላይ ያለውን አክብሮትና እምነት ዝቅ የሚያደርግ ባሕርይ ወይም

ለ. ግዴታን አለመወጣት ወይም የታዘዙትን ተግባር ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆን ወይም

ሐ. ሥራን በሥርዓት፣ በትጋት፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ አለማከናወን ወይም

መ. ሱስ በሚያስይዝ በመድኃኒት ወይም በመጠጥ ተጽዕኖ ምክንያት ሥራን ማከናወን አለመቻል ወይም

ሠ. በሥራ ባልደረባ ወይም በተገልጋይ ላይ የወሲብ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈጸም፣ ማሰገደድ፣ መድፈር ወይም ለመድፈር ሙከራ ማድረግ ወይም ለሌሎች ሰዎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

አንቀጽ 7.ታማኝነት

ታማኝነት ማለት ለሃገሪቱ ህገ መንግስት፣ ህጎችና ደንቦች እንዲሁም ለሚሰራበት መ/ቤት ታማኝ መሆንን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. ህገ መንግሥቱን የማክበርና የማስከበር፣ ለኤጀንሲው ታማኝ የመሆን፣ ሥራቸውን ህግን፣ ደንብን እና የቅርብ አለቆቻቸውና ዋና ዳይሬክተሩ ባጸደቁአቸው መመሪያዎች መሠረት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
2. በአለቃቸው ህገወጥ የሆነ ትዕዛዝ እንዲፈጽሙ ወይም ተገቢ ለሆነ ጉዳይ የተጠየቁትን መረጃ እንዳይገልጹ ከተደረገ ይህንኑ ወዲያውኑ ለኤጀንሲው ኃላፊ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለስነምግባር መኮንኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡
3. በኤጀንሲው ውስጥ ሕገወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያወቁ ወይም ሲመለከቱ ይህንኑ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለሥነምግባር መኮንኑ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የስራ ባልደረቦቻቸው ማጥፋታቸውን ወይም ስራቸውን በሚጠበቀው ሙያዊ ስነምግባር መሰረት አለማከናወናቸውን እያወቁ መደበቅ ወይም መከላከል የለባቸውም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/፣/2/፣/3/ እና /4/ ሥር የተጻፉትን በሚቃረን ሁኔታ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፣

ሀ. በተመሳሳይ ስራ መስክ የተመደበን የሥራ ባልደረባን ብቃት ማነስ እያወቀ ለቅርብ ኃላፊው አለማሳወቅ ወይም ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ማሳወቅ፣

ለ. የሥራ ባልደረባን ህገወጥ ተግባር ወይም የሥነምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ ባሕርይ ለሚመለከተው የስራ ኃላፊ ወይም ለሥነምግባር መኮንኑ አለማሳወቅ ወይም ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ ማቅረብ፣

ሐ. በመንግሥት የፖሊሲ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መረጃን ሆን ብሎ መግለጽ፣ ወይም

መ. ውሳኔን ያለአግባብ ማዘግየት ወይም አንድ ውሳኔ እንዳይፈጸም እንቅፋት መፍጠር፣ ወይም

ሠ. ከአለቃ ወይም ከሌላ ኃላፊ የተላለፈለትን ትዕዛዝ ለማክበር ፈቃደኛ አለመሆን፣

ረ. የስራ ሰዐትን አለማክበር እንዲሁም ሳያስፈቅዱ ከስራ ገበታ ላይ መቅረት፣

ሰ. ከስራ ጋር በተያያዘ ስጦታ ወይም መስተንግዶ መቀበል ወይም ስጦታ የሚቀበል ሰራተኛን ወይም ኃላፊን አይቶ ያለመግለጽ

ያስቀጣል፡፡

አንቀጽ 8.ግልፅነት

ግልጽነት ማለት ተገልጋዩ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲደርሰው ማድረግን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. በህግ መሠረት የመሥራትና ውሳኔዎችን በተቻለ መጠን በግልጽ መስጠት ይኖርባቸዋል፣ ለውሳኔአቸውም ምክንያት ሊኖራቸውይገባል፡፡

2. ህግን በማይቃረን ሁኔታ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

3. የሚሰጡትን አገልግሎት በሚመለከት ከተጠቃሚው ለሚቀርብላቸው የመረጃ ጥያቄ መረጃው በሚስጥር የሚጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡ ለሚያሣልፉት ውሳኔ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

4. በንዑስ አንቀጽ /1/፣/2/፣ እና /3/ ሥር የተጻፉትን በሚቃረን ሁኔታ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

   ሀ. ህጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጃቸው የሚገኘውንና ለሕዝቡ ግልጽ እንዲደረግ ያልተከለከለ መረጃን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም፣

   ለ. ለሚያሣልፏቸው ውሳኔዎች ምክንያት ወይም ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም፣

   ሐ. ለሥራ ግምገማ አግባብነት ያለው አካል ላቀረበላቸው የመረጃ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

   መ. ከደንበኞችም ሆነ ከሰራተኞች ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ወይም ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ አለመስጠት፡፡

አንቀጽ 9.ምስጢር መጠበቅ

ሚስጥር መጠበቅ ማለት ይፋ እንዲወጡ ያልተፈቀዱ መረጃዎችን ያለማውጣትን ይይዛል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ሃላፊዎች፡-

1. ሚስጥራዊ ያልሆነ ወይም ሕዝቡ የሚያውቀውን ወይም ሊያገኘው የሚችለውን መረጃ መደበቅ የለባቸውም፡፡

2. በስራ አጋጣሚ ያወቋቸውንና በሚሥጥር ሊጠበቁ የሚገባቸውን ወይም ግለሰባዊ የሆኑ መረጃዎችን በሚስጥር መያዝ አለባቸው፡፡

3. በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር በሥራ አጋጣሚ ያወቋቸውን ሚሥጥሮች መግለጽ የለባቸውም፡፡

4. የመ/ቤቱን ሥራ ከለቀቁ ወይም ወደሌላ ሥራ ከተዛወሩ በኋላ በሥራቸው አጋጣሚ ያወቁትን ሚስጥራዊ መረጃ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ ፣ /2/ ፣/3/ እና /4/ ሥር የተጠቀሱትን

በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

ሀ.ምሥጢራዊ መረጃን ሆንብሎ ወይንም በቸልተኝነት ሥራ ላይ እያሉ ወይም በቋሚነት ወይም በሌላ አገልግሎት ምክንያት ሥራ ከለቀቁ በኋላ መግለጽ፣

ለ. ምሥጢራዊ መረጃን ለግል ጥቅም ማዋል፣

ሐ. ሚስጥራዊ መረጃን ከጥቅም ውጭ ማድረግ

6. በሚስጥር ሊያዙ የሚገባቸው የመረጃ ዓይነቶች በመ/ቤቱ የውስጥ ደንቦች ይወሰናሉ፡፡

አንቀጽ 10.ሐቀኝነት

ሐቀኝነት ማለት እውነተኛ ሆኖ መገኘት፣ ከአታላይነትና ከአጭበርባሪነት የጸዳ መሆን የሚሉትን ሃሳቦች ይይዛል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ኃላፊዎች፣

1. የመንግሥት ሀብትና አገልግሎቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለሚመለከታቸው ማከፋፈል ወይም ማዳረስ አለባቸው፡፡
2. የገቡትን ቃል የማክበር፣ ቅን የመሆን፣ ከማታለልና ህገወጥ ድርጊት ከመፈጸም ወይም ከሙስና ነጻ የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡ የመንግሥትን የሥራ ጊዜ፣ መገልገያና ሀብት ለግል ጥቅም ማዋል የለባቸውም፡፡
3. ፖሊሲን በሚመለከት የሚያማክሩ ሰራተኞች ትክክለኛና ያልተዛባ ምክር መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ ፣ /2/ ፣ እና /3/ ሥር የተጻፉትን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡
   ሀ. ማጭበርበር ወይም በሥልጣን መነገድ፣ ሰነድ መሰረዝ መደለዝ ወይም ማጥፋት የመ/ቤቱን ማህተም ለህገወጥ ድረጊት መጠቀም፣ ጉቦ መቀበል፣ ጉቦ እንዲሰጡ መጠየቅ ወይም ጉቦ መስጠት፣
   ለ. በመንግሥት አገልግሎቶች ወይም ሀብት ያለአግባብ መጠቀም ወይም

ሐ. ሀሰተኛ ወይም ተገቢ ያልሆነ የአበል ክፍያ ጥያቄ ማቅረብና ከመመሪያ ውጭ አበል መውሰድና አበል መክፈል፣

መ.የሕዝብን ጥቅም በሚጎዳ አኳኋን መሥራት ወይም

ሠ. ሆን ብሎ ሰዎችን ለመወንጀል በሃሰትና መረጃ በሌለበት ሁኔታ በቂም በቀል ተነሳስቶ ጥቆማ ማቅረብ፣

አንቀጽ 11.ተጠያቂነት

ተጠያቂነት ማለት አንድ ሰው ለሚሰራው ስራ፣ ለሚያስተላልፈው ውሳኔና ለሚወስደው እርምጃ ኃላፊ መሆንን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ኃለፊዎች፡-

1. ለሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡በውሳኔዎቹና ባከናወኗቸው ሥራዎች ምክንያት ለሚቀርብላቸው ተገቢ የሆነ የማጣራት ስራ ራሳቸውንዝግጁ የማድረግና በተፈለገ ጊዜ የመቅረብ ወይም የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡
2. የመንግሥትን ፖሊሲ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡
3. ግዴታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ጥያቄ ሲቀርብላቸው አስፈላጊውን ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ ፣ /2/ ፣ /3/ እና ሥር የተገለጹትን በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል

   ሀ.ስላከናወኗቸው ሥራዎች ለሚመለከተው ሰው በወቅቱ ሪፖርት አለማቅረብ ወይም የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ፣

   ለ. የተሰጣቸውን ግዴታ በወቅቱ አለመወጣት ያስቀጣል፡፡

አንቀጽ 12. የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም

የህዝብን ጥቅም ማስቀደም ማለት ማንኛውንም ተግባር የህዝብን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ማከናወንና የጋራ ጥቅምን ማስቀደምን ይይዛል፡፡ በመሆኑም ሠራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና የሚያከናውኗቸው ሥራዎች የሕዝቡን ጥቅም እንጂ የግላቸውን፣ የቤተሰባቸውን ወይም የወዳጆቻቸውን ወይም የሌላ አካልን ወይም ቡድንን ጥቅም የሚያስጠብቁ መሆን የለባቸውም፡፡ የመ/ቤቱን ሥራ ለግል ጥቅማቸው ማዋል የለባቸውም፡፡
2. ከሚሰጧቸው ውሣኔዎችና ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭትን ለመፍጠር የሚችሉ ሁኔታዎችን አስቀድሞ ማሣወቅ/መግለጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. በመንግሥት ሥራ ላይ እያሉ ከመደበኛ ሥራቸው ጋር ሊጋጭ የሚችል ሌላ ሥራ መሥራት የለባቸውም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ ፣ /2/ ፣ /3/ ሥራ የተጻፉትን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋት መፈጸም ያስቀጣል፡፡

ሀ.የግል ወይም የሌሎች ቡድኖችን ጥቅም ከሕዝብ ጥቅም ማስበለጥ ወይም

ለ.የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት አለማሣወቅ ወይም አለመግለጽ፣

ሐ.ከተቀጠረበት መ/ቤት ውጭ ያለፈቃድ ተቀጥሮ መሥራት

አንቀጽ 13.ሥልጣንን በአግባቡ መጠቀም

ስልጣንን በአግባቡ መጠቀም ማለት በህግ ተወስኖ የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም

ኃላፊነትን መወጣትን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሠራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. ከሚያከናውኗቸው ሥራ ጋር በተያያዘ የመወሰን ሥልጣን አላቸው፡፡ በዚህ ሥልጣን መገልገል የሚቻለው ለመ/ቤቱ በሕግ ተወስኖ በተሰጠው መሠረት መሆን አለበት፡፡ በሥልጣናቸው ያለአግባብ መገልገል አይችሉም፡፡
2. በማስገደድ ወይም ተፅዕኖ በማድረግ ሌሎች ሰዎች ገንዘብ እንዲያበድሩዋቸው ወይም ዕቃ እንዲገዙላቸው ወይም የዋጋ ቅናሽ እንዲያደርጉላቸው ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም እንዲሰጡዋቸው መጠየቅ የለባቸውም፡፡
3. ሕግን መሠረት በማድረግ ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ኃላፊነታቸውን የግል ጥቅም ለማግኘት ማዋል የለባቸውም፡፡
5. ስልጣናቸውን ተጠቅመው በስራቸው ያሉ ሰራተኞችን ከመመሪያና ደንብ ወጭ እንዲሰሩ ማዘዝና መገፋፋት የለባቸውም፡፡
6. ለስራ ባልደረቦቻቸው ወይም ለተገልጋዮች አማላጅ ሆነው ጉዳይ ማስፈጸም የለባቸውም፡፡
7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /6/ሥር የተጻፉትን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

ሀ.ከስልጣን በላይ መስራት ወይም የአሰራር ስርአቶችንና ደንቦችን በመጣስ መስራት፣

ለ. በሰራተኞች ላይ ጫና በመፍጠር ሰራተኞች ህገ ወጥ ተግባር እንዲፈጽሙ ማዘዝ፣ አግባብ ባልሆነ መንገድ አማላጅ ሆኖ ጉዳይ ማስፈጸም፣

ሐ.ተገቢ ጥንቃቄ ሳያደርጉና የሌሎች ሰዎችን መብቶች ከግንዛቤ ሳያስገቡ መስራት፡፡

አንቀጽ 14.አድልዎ አለመፈጸም

አድሎ አለመፈጸም ማለት ሰዎችን በእኩል አይን ማየትና በሰዎች መካከል ልዩነት ያለመፍጠርን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ሠራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ውሣኔ የመስጠትና ሥራቸውን የማከናወን ግዴታ አለባቸው፡፡
2. አድልዎ በሌለበት ሁኔታ የመሥራት፣ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር/ ብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ/በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ወይም አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሣያደርጉ በቀረበላቸው ጉዳይ ፍሬነገር ላይ ብቻ ተመስርተው ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
3. በአድልዎ በመሥራት የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

   ሀ. የጉዳዩን ፍሬነገር ከግምት ውስጥ ያላስገባና አንድን ቡድን ወይም ግለሰብ ለመጥቀም ህጋዊ ያልሆነ ምክር መስጠት ወይም

   ለ .ከህግና መመሪያ ወጭ የሆነ ቅጥር፣ ዕድገት፣ ስልጠና ወይም የትምህርት እድል መስጠት፣

   ሐ.በትውውቅ፣ በጾታ፣ በቀለም፣ በብሄር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት፣ በዝምድና፣ በኃላፊነት ደረጃ ምክንያት በደንበኞች ወይም በሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ

አንቀጽ 15.ሕግን ማክበር

ህግን ማክበር ማለት የህግ የበላይነትን በማክበር ስራን ህግ በሚፈቅደው መሰረት ብቻ ማከናወንን ያካትታል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. ሕገ መንግሥቱና የሀገሪቱን ሕጎችን የማክበር እና የማስከበር አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ሕገች እና ሥልጣን ባላቸው ኃላፊዎች በተሰጠው ትዕዛዞች መሠረት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

2. ኃላፊዎች የሚሰጡት መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ሕገወጥ ወይም ተገቢ ካልሆነ መመሪያውን ወይም ትዕዛዙን ለሰጠው ኃላፊ ይህንኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

3. ኃላፊዎች ህገ ወጥ ወይም ተገቢ ያልሆነ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ለሰራተኞች ማስተላለፍ የለባቸውም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /3/ ሥር የተጻፉትን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

   ሀ. ሕጎችን መመሪያዎችንና ትእዛዞችን አለማክበር፣

   ለ. ሌሎች ሠራተኞች ወይም ሰዎች ሕጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን እንዳያከብሩ ማነሳሳት ወይም

   ሐ. ከሕግ ውጭ መሥራት ወይም

   መ. ሌሎች ሰዎች ከሕግ ውጭ እንዲሰሩ መፍቀድ ወይም ማገዝ፣

ሠ. በስራ አካባቢ አምባጓሮ ወይም ጠብ በመፍጠር ወይም ባለጉዳይን ወይም ኃላፊን ወይም የስራ ባልደረባን መስደብ ወይም መደባደብ፣

ረ. የመ/ቤቱን ባጅ ወይም መታወቂያ ህገወጥ ለሆነ ተግባር መጠቀም፣

ሰ. የግዥና የሽያጭ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ነክ ስራዎችን ህግ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት አለመፈጸም፣

ሸ. ያልተፈቀዱና በህይወትና በንብረት ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ መሳሪያዎችና አደንዛዥ ዕጾችን ይዞ መግባት፣

አንቀጽ 16. ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት

ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ማለት ሕዝብን በአክብሮት የማገልገል ስሜትና ባህሪይን መላበስ የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ሠራተኞችና ኃላፊዎች፡-

1. ባለጉዳዮችን በጥሞና በማድመጥ፡ በማክበር እና በትህትና ለጥያቄዎቻቸው በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ ወይም መፍትሄ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

2. የሕዝብ አገልጋይነት መርህን ወይም ግዴታን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል

ሀ. ለባለጉዳይ ተገቢ ትህትና አለማሳየት ወይም ተገቢ ባልሆነ አኳኋን ማስተናገድ፣

ለ. ተገልጋይ/ ደንበኛን ስለመብቶቹ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ፣

ሐ. ከባለጉዳይ ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ከሚገባው በላይ ማዘግየት ወይም ተገቢውን ምላሽ አለመስጠት

አንቀጽ 17. አርአያነት

አርአያ መሆን ማለት በመልካም ሥነምግባር ለሰራተኛውም ሆነ ለተገልጋዩ አብነት በመሆን ግንባር ቀደምና ምሳሌ መሆንን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡-

1. የመንግሥትን ሥራ በሚያከናውኑበት ማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ግንባር ቀደምና ምሳሌ በመሆን የሚጠበቅባቸውን ከፍ ያለ አርአያነት በማሳየት በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን መርሆዎች ማኅልበትና በተግባር እንዲተረጎሙ ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

2. የኃላፊነት ስሜት የሚሰማቸው የተሻለ ለውጥን የሚደግፉ፡ የመ/ቤቱን መልካም ስም የሚጠብቁና የአሠራር ባህል እንዲዳብር መተማመን ሥር እንዲሰድና ጸንቶ እንዲቆይ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ሥር የተጻፉትን በመጣስ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ኃላፊነት ወይም የቅጥር ቀደምትነት ያለው የመንግሥት ሠራተኛ በስራ ክፍሉ ከሲቪል ሰርቪሱ የሚፈለጉትን የመ/ቤቱን አሰራር ወይም የሥነምግባር መርሆችን ለሥራ ባልደረቦቹ ካላሳወቀ፣

ለ. የሥራ ኃላፊንና ሌሎች ሠራተኞችን መልካም ሥነምግባርን በተላበሰ መልኩ ካላስተናገደ ይቀጣል፡፡

ክፍል ሦስት

በዲሲፕሊን የሚያሰቀጡ፣ የስነምግባር ጥፋቶችና እርምጃዎች

አንቀጽ 18.የዲሲፕሊን ቅጣትና አፈጻጸም

1. ኤጀንሲው በኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ የሚወስደው የዲሲፕሊን እርምጃ ዓላማው ሠራተኛው በፈጸመው ጥፋት ተጸጽቶ እንዲታረምና ለወደፊቱም ስራውን በመልካም ምግባር ለማከናወን እንዲችል ለማስተማርና የማይታረም ሆኖ ሲገኝ እርምጃ ለመውሰድ ነው፡፡

2. በኤጀንሲው ሰራተኞችና ኃላፊዎች ላይ የሚወሰደው የዲሲፕሊን አርምጃ አፈጻጸም፣

ሀ/የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ ባለመፈጸማቸው ወይም ማድረግ የማይገባቸውን በማድረጋቸው ስለጥፋታቸው በፍትሐብሔር ወይም በወንጀል ተጠያቂነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ላደረሱት ጥፋት ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ኤጀንሲው ባለው የስነምግባር መመሪያ መሠረት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

ለ/ በሥነ ምግባር ግድፈት የሚወሰነው ቅጣት ማንኛውም ፍ/ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ሳይጠብቅ ሊፈጸም ይችላል፡፡

ሐ/ የሥነ ምግባር ግድፈት የፈጸመ ማንኛውም ሠራተኛ ድርጊቱ በዚህ የሥነ ምግባር መመሪያና በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ላይ የተመለከተ ሆኖ ሲገኝ በአንድ ጊዜ በሁለቱም በተደራራቢነት ሊቀጣ አይገባውም፡፡

አንቀጽ 19.ቀላል የስነምግባር ግድፈቶች

በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት፡

አንቀጽ 6 (ሐ)፣አንቀጽ7(5) (ሀ)(ረ)፣አንቀጽ 8 (4) (ሀ) (ለ) (ሐ) (መ)፣ አንቀጽ 10 (4) (ለ) (ሠ)፣ አንቀጽ 11 (4) (ለ)፣ አንቀጽ 12(4) (ለ)፣ አንቀጽ 13(7) (ሐ)፣ አንቀጽ 14(3) (ሀ) አንቀጽ 16 (2) (ለ)፣አንቀጽ 17(3) (ሀ) (ለ) ስር የተዘረዘሩት ጥፋቶች ቀላል ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው፡፡

እነቀጽ 20.ከባድ የስነምግባር ግድፈቶች

1. በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6(ሀ) (ለ) (መ)፣አንቀጽ7 (5) (ለ) (ሐ) (መ) (ሠ) (ሰ) ፣አንቀጽ 9(4) (ሀ) (ለ) (ሐ) ፣ አንቀጽ 10 (4) (ሀ) (ሐ) (መ) ፣ አንቀጽ 11 (4) (ሀ) ፣ አንቀጽ 12(4) (ሀ) (ሐ) ፣ አንቀጽ 13 (7) (ሀ) (ለ)፣ አንቀጽ 14 (3) (ለ) (ሐ)፣ አንቀጽ 15(4) (ሀ) (ለ) (ሐ) (መ) (ሠ) (ረ) (ሰ) (ሽ)፣ አንቀጽ 16(2) (ሀ) ስር የተዘረዘሩት ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው፡፡

2. ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ መፈጸም ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ያስከትላል፡፡

አንቀጽ 21.የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶችና አመዳደብ፣

ሀ/ 1. ቃል ማስጠንቀቂያ፣

2. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣

3. እስከ አንድ ወር የሚደርስ የደሞዝ ቅጣት

4. እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የደሞዝ ቅጣት

5.እስከ ሁለት አመት ድረስ ሊቆይ የሚችል ከስራ ደረጃና ከደሞዝ ዝቅ ማድረግ

6. ከስራ መሰናበት

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ (ከ1-3) የተዘረዘሩት ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች ሲሆኑ ፣ (ከ4-6) ተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች ናቸው፡፡

ሐ/ አንድ ጥፋት በዚህ መመሪያና በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሰረት ይታያል፡፡

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 22.ጥቆማን ስለማሳወቅ

ሀ/ ማንኛውም ሠራተኛ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ መርሆችን የሚጻረር የሥነምግባር ጉድለት መፈጸሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለመስሪያቤቱ ኃላፊ፣ ለስነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ከበድ ያለ ከሆነም ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ/ የሚያቀርበው ጥቆማ አውነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የፀዳ፣ አሳሳች ያልሆነና ምክኒያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሰረተ መሆን የኖርበታል፡፡

ሐ/ ጥቆማ አቅራቢው ከማንኛውም በቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

መ/ ጥቆማ አቅራቢው ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ በምስጢር መያዝ አለበት፡፡

አንቀጽ 23.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ኃላፊና ሠራተኛ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለስራው የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን መረጃና ሌላ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 24.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ እና የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 25.መመሪያ ስለማሻሻል

ኤጀንሲው ይህንን መመሪያ ለማሻሻልልም ሆነ አዲስ መመሪያ ለማውጣት ይችላል፡፡

አንቀጽ 26.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡